# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

26



ፓርቲ የሌለው ወዝአደር አዝማች
እንደሌለው ሠራዊት ነው ።

ግንቦት ፲፭ — ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

## ርእሰ አንቀጽ

# አብዮታችን ፤ አንድነታችንና ዘመቻው

የኢትዮጵያ አብዮታውያን የሀገራችንን አንድነትና ህልውና ከጠቅላላው ከኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ገንጥለው የተመለከቱበት ወቅት የለም ። ከዚህ ቀደምም ፤ ዛሬም ሆነ ወደፊት የአብዮታውያን ትግል የጭቁኖችን የትግል ክንድ አስተባብሮ የጋራ ጠላትን በጋራ ትግል ለመደምሰስና ሀገራችን ብሔረሰቦቿ በሙሉ በእኩልነት ያበቡባትና ያሸበረቁባት ነፃና ኩሩ ሀገር እንድትሆን ነው ።

ወደዚች ነፃና ኩሩ አገር በሚደረገው ረዥም ጉዞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች እስካሁን ድረስ ብዙ ውጣ ውረድ አጋጥሟቸዋል ። ወደፊትም ገና ብዙ መከራና መሥዋዕትነት እንደሚጠብቃቸው ያውቃሉ ። ዞሮ ዞሮ ግን በየጊዜው ከተጨባጩ ሁኔታ እየተነሡና ታክቲካቸውን እየቀየሱ በቆራጥነት እስከታገሉ ድረስ የመጨረሻው ድል የነሱ ለመሆኑ ምንም ጥርጣሬ ሊኖር አይችልም።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት እጅግ ገፍቶ መሔዱና የዚያኑ ያህል ደግሞ ጠላቶቹ ኃይላቸውን አስተባብረው ትግላቸውን እንዳፋፋሙ ገሃድ ነው ። የውስጥ ጠላቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ አድኃሪና ፀረ አብዮት ኃይሎች ጋር በአንድነት ቆመዋል ። የኢትዮጵያ አብዮት ወዳጆችም የአብዮታችንን ገጥታ በሚገባ ተገንዝበው ድጋፍ ለመስጠት ተነሥተዋል ።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት ብዙ ችግሮች አሉበት ። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በፀረ ኮሚኒስት ኒሜሪ አጋፋሪነት በሀገራችን ዳር ድንበር ላይ ብቻ ሳይሆን ውስጥ እየገቡ በአብዮቱ ላይ ለሚያምፁ አድኃሪ ኃይሎች የመሣሪያ ፤ የገንዘብ ፤ የሰው ድጋፍ ማስተላለፊያ ሆኗል ። በኤርትራ ክፍለ ሀገር ለአድኃሪ ተገንጣዮች አባሪ ተባባሪ በመሆን በይፋ ሰፊ የሆነ ርዳታ ያበረክታል ። የአፋርና ኢሳ ግዛት ሕዝብ በምንም ዓይነት በማያሻማ ሁኔታ ነፃነቱን መርጧል ። አዲሲቱ ኢትዮጵያ ለዚህ ነፃነት በግንባር ቀደምነት ታግላለች ። ይህንንም ነፃነት ሙሉ በሙሉ እንደምታከብር አስታወቃለች ። የሱማሌ ገዥዎች ግን በጅቡቲ ላይ ያላቸውን የመስፋፋት ፍላጐት እስካሁን አላነሱም ። በተጨማሪም የሶማሊያ ገዥዎች በምሥራቅና በደቡብ ኢትዮጵያ እያስታጠቁ የሚልኳቸው ሰርጎ ገቦች አሁንም በዚያ አካባቢ ከመለዮ ለባሹና ከአርሶ—አደሩ ጋር በመዋደቅ ላይ ይገኛሉ ። በመሐል አገር ቢሮክራሲውን መሽገው የሚያሤሩ የኢ. ዲ. ዩ. ፤ የኢ. ሕ. አ. ፓ. ና የኢ. ኤል. ኤፍ. ወኪሎች ኃይላቸውን እያስተባበሩ ከመታገል ወደኋላ አላሉም ። እነዚህና ሌሎችም የኢትዮጵያ አብዮትና አንድነት ጠላቶች በተለይ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምንና የዘይት ዶላር ያሰከራቸውን የሳውዲ ዓረብያ ነገሥታትን ርዳታ ስለሚያገኙ ገና ለረዥም ጊዜ አብዮታችንንና አንድነታችንን መፈታተናቸውን እንደሚቀጥሉ አያጠራጥርም ።

ነገር ግን ጠላቶቻችን ምን ያህል ኃያል ቢሆኑና ትግሉም ምን ያህል ጊዜ ቢወስድ ዞሮ ዞሮ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ከሁሉም በላይ በገዛ ኃይላቸው ተማምነው በቆራጥነት እስከታገሉ ድረስ ድልን መቀዳጀታቸው የታወቀ ነገር ነው ። ሰሞኑን የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀ መንበር ሀገራችን ያጋጠሟትን የተወሳሰቡ ችግሮች በመጥቀስ የአብዮታዊት እናት



አገር ጥሪን ካስተላለፉ ወዲህ የሚታየው ከፍተኛ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመታገልና ለመሠዋት ሙሉ በሙሉ ዝግጁ እንደሆነ አስመስክሯል ።

ለዚህ ትግል ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር የተንቀሳቀሰበት መፈክር «አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት» የሚል ነው ። ይህ ምን ማለት ነው ? ይህ ማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከብዝበዛና ከጭቆና ጨርሶ ለሚያላቅቀውና አዲስ ኑሮ ለሚያስጨብጠው አብዮቱ ለመሞት ዝግጁ ነው ማለት ነው ። ግን ይህ ብቻ አይደለም ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚህች ታሪካዊና ውድ እናት አገሩ አንድነት ፤ ክብርና ነፃነትም ለመሞት ዝግጁ ነው ማለት ነው ።

ዛሬ በኢትዮጵያ የሚካሔደው ትግል ከተሰበጣጠሩ አቅጣጫዎች የሚሰነዘር ጥቃትና የተሰበጣጠሩ ዓላማዎች ያሉት ቢመስልም ፤ ዞሮ ዞሮ በአብዮትና በፀረ አብዮት መሐከል የሚደረግ ትግል ነው ። የአብዮቱ ሠፈር ኃይሎች አብዮታቸውን ከግብ አድርሰው የተለያዩ ብሔረሰቦች ያበቡበትና ያሸበረቁበት ፤ የጭቁን ሕዝቦቿ አንድነት ኅብረት የጠነከረበት ፤ በዓለም ነፃ ሕዝቦች ሸንጐ የታፈረችና የተከበረች ነፃ ፤ ኩሩ ፤ ሀብታም ፤ ጠንካራ አገር ለመገንባት ይታገላሉ ከነዚህ ዓላማዎች አንዱ ከተዛነፈ ፤ አንዱ ካልተሟላ አብዮታችን ግቡን መታ ማለት አይቻልም።

ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የኢትዮጵያ አብዮትና የኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ በምንም ዓይነት የማይነጠሉ ናቸው ። አብዮታችንን የሚፃረሩ ኃይሎች አንድነታችንን ከሚፃረሩ ኃይሎች ጋር ይተባበራሉ ። በመጀመሪያ ኢ. ሕ. አ. ፓ. ከዚያም በኋላ የመሳፍንቱ ኢ. ዲ. ዩ. ለኤርትራ ተገንጣዮች ሙሉ የሆነ ድጋፍ መስጠታቸው ፀረ አብዮት ኃይሎች የኢትዮጵያን አንድነት እንደሚፃረሩ ማረጋገጫ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ፀረ አንድነት የሆኑት የኤርትራ አድኃሪ ተገንጣዮች ከነኢ. ዲ. ዩ ፤ መተባበራቸው ዛሬ የኢትዮጵያን አንድነት የሚፃረሩት ኃይሎች ምን ዓይነት የመደብ አቋም እንዳላቸው ቁልጭ አድርጐ ያስረዳል ።

ባጭሩ በዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔታ ፀረ አብዮት የሆኑ ኃይሎች ሁሉ ፀረ አንድነት ናቸው፤ ፀረ አንድነት የሆኑ ኃይሎች ደግሞ አድኃሪ ኃይሎች ናቸው ። ከዚህ የምንማረው ሐቅ አለ ። ይኸውም የኢትዮጵያ አብዮታውያን ለሀገራቸው አንድነትና ለአብዮታቸው መግፋት የሚያደርጉትን ትግል በአንድነት አያይዘው ማየታቸው ትክክለኛ አመለካከት መሆኑን ነው ።

ስለሆነም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአብዮታዊት እናት አገር ጥሪውን ተቀብሎ ለዘመቻ መንቀሳቀሱ አብዮታውያን በሙሉ የሚደግፉት ነው ። ሰሜን ኢትዮጵያ የመሳፍንትና የፀረ አንድነት ኃይሎች ምሽግ እንዳትሆን ማድረግ የጠቅላላው የኢትዮጵያ ጭቁኖች ተግባር በመሆኑ ፤ ከመላ ኢትዮጵያ ጭቁኖች የተውጣጣ አብዮታዊ ጦር የተፋፋመ የመደብ ትግሉን ወደነዚህ ክፍላተ ሀገራት ለማዛመት በሚዘጋጁበት በአሁኑ ወቅት ስለዚህ አብዮታዊ ዘመቻ አንዳንድ መሠረታዊ የሆኑ ሀቆችን መሰንዘር ያስፈልጋል ።

ከሁሉ አስቀድሞ ይህ ዘመቻ አብዮታችንንና አንድነታችንን ከፀረ ሕዝብ ኃይሎች ተከላክሎ ለማዳን የሚደረግ የአብዮታዊ ትግላችን የማይነጠል አካል ነው ። ስለሆነም ዘመቻው የረዥም ጊዜና መራራ እንደሚሆን ፤ በጠቅላላው በሀገሪቱ የሚደረገው ፀረ ፊውዳል ፀረ ኢምፔሪያ

ሊስትና ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ትግል ድልን ሳይቀዳጅ ብቻውን ሊፈጸም የማይችል ትግል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልገናል ።

ይህንን የረዥም ጊዜ መራራ ትግል ሐሳብ መቀበል ስለዘመቻው ግልጽ የሆነ አመለካከት እንዲኖረን ይረዳናል ። ይኸውም ማለት የዘመቻው የፖለቲካና የጦር መልኩ እጅግ የተያያዙና ዲያሌክቲካዊ በሆነ መንገድ የተሣሠሩ መሆናቸውን ያስገነዝበናል ። አብዮታችን ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቀፈው የደገፈው ሊሞትለትም የተሰናዳለት አብዮት ነው ። የአብዮታችን ኃያልነት፤ የአብዮታችን የማይበገር መሆን እዚህ ላይ ነው ። ስለሆነም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህ ዘመቻ የጠቅላላው የአብዮታዊው ትግል አካል እንደሆነ እንዲያውቀው ያስፈልጋል ። እንደዚህም በመሆኑ በግንባር የሚሰለፈው ዘማች ብቻ ሳይሆን ፤ በጠቅላላው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በያለበት ሙሉ በሙሉ የሚሳተፍበትና ሊሳተፍበት የሚገባው ዘመቻ መሆኑን እንዲያውቀው ያለማቋረጥ መቀስቀስ ይኖርበታል ። ባጭሩ ሁሉም በያለበት ምርቱን በማሳደግ፤ ፀረ አብዮት ኃይሎችን እየመነጠረ በመደምሰስ፤ የመደባችንን ትግል በማፋፋም በግንባር ቀደምትነት ለዘመተው ጦር የሚያስተማምን ደጀን መሆን ይኖርበታል ማለት ነው ።

ዘመቻው የአብዮታዊ ትግላችን አካልና የረዥም ጊዜ ትግል ነው ማለት ራሱን ዘማቹን ሠራዊት በሚመለከተው በኩል አንዳንድ ተግባራትን ይጥልብናል ። ለአብዮቱና ለእናት አገሩ ህልውና በሚደረገው ትግል ዘማቹ ሠራዊት ማንኛውንም መሥዋዕትነት ለመቀበል ዝግጁ የሚያደርገው የማያቋርጥ የፖለቲካ ትምህርት እንዲሰጠው ያስፈልጋል ። በተለይም ለምን እንደሚዋጋ ፤ ማንን እንደሚዋጋና በመጨረሻም የወሰደውን ጊዜ ቢወስድ ድሉ የሰፊው ሕዝብ እንደሆነ እንዲገነዘብ በሚገባ ማስረዳት ያስፈልጋል ። ለረዥም ጊዜ ተጋድሎና መሥዋዕትነት ብቁ የሚያደርገው ይህ ያለማቋረጥ የሚሰጠው የፖለቲካ ንቃት ብቻ ነው ።

ይህንን ዘመቻ እንደአብዮቱ አካል መውሰድ ሌላም የሚያስከትለው ተግባር አለ ። በሰሜን ኢትዮጵያ በተለይም በኤርትራ የሚገኙ ጭቁኖችና ተራማጅ ኃይሎች በዚህ ትግል ውስጥ በሚገባ እንዲሳተፉ ያልተቋረጠ የቅስቀሳና የማደራጀት ትግል ማካሔድ ያስፈልጋል ። በተለይ ኤርትራን በሚመለከት በኩል በዚያ የሚገኙ ተራማጆች በአሁኑ ጊዜ የዚህችን ክፍለ ሀገር ከኢትዮጵያ መገንጠል የሚፈልጉ ኃይሎች እነማን እንደሆኑ እንዲያጤኑ መጣር ያስፈልጋል ። የኤርትራ ሰፊ ሕዝብም በጠቅላላው ፀሀገሪቱ የሚካሔደውን አብዮት ማንነት እንዲረዳ እሱም በሙሉ ልቡ በዚህ በመጣለት አብዮት ውስጥ እንዲሳተፍ ፤ አድኃሪ የዓረብ መንግሥታት ዛሬ ኤርትራን ለመገንጠል የሚታገሉት ለምን እንደሆነ እንዲያውቀውና በአብዮቱ ሠፈር ጸንቶ እንዲታገል ማድረግ ያስፈልጋል ።

ባጭሩ ለማጠቃለል የዘመቻው ዓላማ በምንም ዓይነት የማይነጣጠሉትን የአብዮታችንንና የእናት አገራችንን ህልውና በማረጋገጥ ነው ። በዛሬው ወቅት የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች አንድነታቸውን እንደነፃነታቸውና እንደ ብሔራዊ ክብራቸው ከፀረ አብዮት ኃይሎች በግድ ነጥቀው መውሰድ እንዳለባቸው እንዲያውቁት ያስፈልጋል ። ለአንድነታችን የሚደረገው ትግል የሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ ይጠይቃል ። የዘማቹን ሠራዊት ከፍተኛ የፖለቲካ ንቃት ይፈልጋል ። በኤርትራ ክፍለ ሀገር የሚገኙ ተራማጆችና ጭቁን ሕዝቦችም ነቅተውና ተደራጅተው እንዲሳተፉበት መታገል ያስፈልጋል ።

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው ።